ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው
ወገኖች የጤናው ሴክተር ምላሽ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

**የጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር**

2009 ዓ.ም

**የተሳታፊ ማንዋል ⌖ ሞጁል አንድ**

# ስርአተፆታ እና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መግቢያ



# ምስጋና

ይህ የስልጠና ማንዋል የምክክር ሂደትና የሰነድ ምርመራ ውጤት ነው፡፡የአለም የጤና ድርጅት የኢትዮጵያ ቢሮ የዚህን የስልጠና ማንዋል የህትመት ወጪ ጨምሮ ለሰጠው የቴክኒክና የአርትኦት ድጋፍ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አድናቆቱንና ምስጋናውን ይገልፃል፡፡ የስልጠናውን ፓኬጅ በማዘጋጀት ሂደት ለተካሄዱት ተከታታይ የምክክር ስብሰባዎች የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ለአደገረው አይካፕ ኢትዮጵያም ሚንስቴር መ/ቤቱ የተለየ አድናቆቱን ይገልፃል፡፡

ይህንን ማኑዋል ለማጠናቀቅ በተለያዩ ደረጃዎች ተሳትፎ ላደረጉት የሚከተሉት ግለሰቦች በተለየ አድናቆታችንን እንገልፃለን፡፡

| | |
|---|---|
| ያምሮት አንዱአለም | በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር - የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር |
| ፍቅር መለሰ (ዶ/ር) | የአለም የጤና ድርጅት - ኢትዮጵያ |
| ሰናይት በየነ (ዶ/ር) | አይካፕ - ኢትዮጵያ |

<u>ፅሁፍ ያበረከቱ፡-</u>

| | |
|---|---|
| ልኡልሰገድ ሊበን | የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ፍትህ ሚኒስቴር |
| ቴዎድሮስ ታምራት | ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር/ፓዝፋይንደር |
| ሄራን አበበ | ፓዝፋይንደር አይ.ኤፍ.ኤች.ፒ |
| ነጋሽ ቱሉ (ዶ/ር) | አይካፕ - ኢትዮጵያ |
| ፍቅርተ ሲዳ | ሲ.ዲ.ሲ  ኢትዮጵያ |
| መኮንን በለጠ | ኤፍ.ኤስ.ሲ.ኢ - አዳማ ፕሮግራም ማስተባበሪያ ቢሮ |
| ካትሪን ካይዘር | በአለም የጤና ድርጅት- ኢትዮጵያ የተ.መ.ድ አለምአቀፍ ወጣት በጎፈቃደኛ |

የሽፋን ገፅ ዲዛይን በአቶ ሄኖክ እጅጉ፣ የአለም የጤና ድርጅት - ኢትዮጵያ

ይህ የስልጠና ፓኬጅ ይጠናቀቅ ዘንድ በሙከራ ስልጠና ወቅት የተሳተፉትን የጤና ባለሙያዎች ላበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ አድናቆታችንን እንገልፃለን፡፡

# መልእክት

የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማሳካትከአለምአቀፍ የዘላቂ ልማት ግቦች አጀንዳ ጋር በእጅጉ በሚደጋገፈውሁለተኛው ሀገራዊ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (GTP II) ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠውናልዩ ትኩረት የሚገባው ነው፡፡ይህንን ግብ ለማሳካት ቁልፍ ተግዳሮት የሚሆነው በተለይ በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚፈፀመውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃትን(GBV/SV) መዋጋት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በስርዓተ-ፆታ እና በጤና መካከል ወሳኝ ቁርኝት መኖሩን ቀደም ብሎ የተገነዘበ ሲሆን ይህንንም ተከትሎ በጤናው ሴክተር ውስጥ የስርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን ጉልህ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡አራተኛው ዙር የጤና ልማት መርሀግብር(HSDP IV) እና በርካታ እስትራቴጂዎችና መመሪያዎች የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርከስርዓተ-ፆታ እኩልነትና ከስርዓተ-ፆታ ፍትሀዊነት ጋር በተያያዘ የጤናውን ዘርፍ ምላሽ ለማሳደግ የወሰዳቸው እርምጃዎች ማሳያዎች ናቸው፡፡


የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተለይም በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ለሚፈፀመው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የጤናውን ዘርፍምላሽ በሰፊው የማስተዋወቅና የማጠናከር ጉልህ ጥረቶችን አድርጓል፡፡
ዋነኛውና በመካሄድ ላይ የሚገኘው ጥረት የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎቶችንማሻሻል ሲሆን ይህም ሴቶች፣ ልጃገረዶችና ታዳጊ ወንዶች የጤና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡ለጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት የስርዓተ-ፆታ እኩልነትንየማበረታታት ስራ በእርግጥም በግልፅ ከተጠቀሱትየጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አላማዎች ውስጥ አንደኛው ነው፡፡

የስርዓተ-ፆታን ግንዛቤና የጤናው ዘርፍ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት የሚሰጠውንአጠቃላይ ምላሽ ከማጠናከር አንፃርደረጃውን የጠበቀናብቃት-ተኮር ሀገራዊ የስልጠና ፓኬጅ መዘጋጀቱሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት መዛባትን ለመቀነስ የገባውን ቁርጠኝነት የሚያግዝ ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡
በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት አሀዶችናበከፍተኛየጤና ተቋምለሚገኙናለሁሉም የጤና ካድሬዎችተገቢውን ስልጠና በመስጠት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሚሰጠውን ውጤታማና ሁሉንአቀፍ የጤና ምላሽ እንደሚያሳካ እናምናለን፡፡

በስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት"የሴቶች ጉዳይ"ብቻ ሳይሆንወንዶችና ታዳጊ ወንዶችም ጭምር የሚጎዳነው፡፡ጥቃትየደረሰባቸው ሰዎችከጥቃቱ እንዲያገግሙና ተመልሰውወደማህበረሰቡእንዲቀላቀሉ ለማድረግ ውጤታማ የህክምና ምላሽ ከመስጠትና አብሮም ስነ-ልቦናዊ ክብካቤና ማህበራዊ ድጋፍ ከማድረግ ጎን ለጎን ስለጉዳዩ ማስተማርና ግንዛቤ መፍጠር፣ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከያ ዘዴዎች/እስትራቴጂዎችን ማሻሻልና ተራማጅ የባህሪይ ለውጦችን ማምጣትና ማስቀጠል ወሳኝነት አለው፡፡

ስርዓተ-ፆታን መሰረትያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች አማካኝነት በማህበረሰብ ውስጥ የመከላከሉ ተግባርሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዋነኝነት ከሚከተላቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡የጤና ባለሙያዎች የስርዓተ-ፆታና የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ፅንሰሀሳቦችን በተመለከተ ያላቸውንግንዛቤና እውቀት ማሻሻል እንዲሁምስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች በመለየትና በመንከባከብ ረገድ ያላቸውን ተጨባጭ ክህሎት ማጠናከር ከፍተኛ የመከላከል ሚና እንዳለውይታመናል፡፡የስልጠና ፓኬጁለጥቃቱ ተጎጂዎች የሚደረገውን የህክምና አሰጣጥ ህክምናዊ ገፅታዎች ማሳደግ ብቻ ሳይሆንየጥቃቱን ተጎጂዎች በስኬታማነት መልሶ ለማብቃትና ውጤታማ የመከላከል ዘዴዎችን/እስትራቴጂዎችን ለመንደፍ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መሰረታዊ መንስኤዎችና የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች የመገንዘብ አስፈላጊነትን አፅንኦት ይሰጥበታል፡፡ከእነዚህ አላማዎች ጋር በተጣጣመ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የዘርፈብዙ አቀራረብን እና የሪፈራል ስርአትን ሚና ማጉላትና ማጠናከር ሌላው የዚህ የስልጠና ፓኬጅ አላማ ነው፡፡

ይህንን የስልጠና ፓኬጅ በማዘጋጀት ሂደት ተባባሪ አዘጋጆች ለሰጡን ድጋፍ ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ ለዚህ የስልጠና ፓኬጅ ዝግጅት፣ አርትኦት፣ ዲዛይንና ህትመት የአለም የጤና ድርጅት የኢትዮጵያ ቢሮ ለሰጠው ድጋፍ ልዩ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን፡፡



ዶ/ር ከበደ ወርቁ
የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስቴር ዲኤታ

## ይህ ሰነድ በሚኒስቴሩ መፅደቁን ስለማሳወቅ

የኢትዮጵያ ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የስራ ላይ ስልጠናዎች ሀገራዊ የጥራት ደረጃን ያሚሉና ተቋማዊ እንዲሆኑ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለጤናው ሴክተር ብሔራዊ የስራ ላይ ስልጠና መመሪያና የአተገባበር መምሪያ አዘጋጅቷል፡፡ መመሪያው የስራ ላይ ስልጠና ሰነዶች ጥራት እንዲጠበቅ ማንኛውም የስራ ላይ ስልጠና ሰነድ በአተገባበር መምሪያው ላይ የሰፈሩትን እስታንዳርዶች/መስፈርቶች ማሚላት እንዳለበት ያስገድዳል፡፡ በዚህም መሰረት ሚኒስቴሩ በስራ ላይ ስልጠና የአተገባበር መምሪያ ላይ አባሪ የሆነውን የስራ ላይ ስልጠና ጥራት ማረጋገጫ ዝርዝር መስፈርት በመጠቀም ማሰልጠኛ ሰነዶችን ገምግሞ ያፀድቃል፡፡

የብሔራዊ የስራ ላይ ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ሂደት አካል በመሆን ይህ **ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች የጤናው ዘርፍ ምላሽ** የስራ ላይ ስልጠና ፓኬጅ የጥራት ማረጋገጫ ዝርዝር መስፈርትን በመጠቀም ተገምግሞ ህዳር 2009 ኣ.ም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፀድቋል፡፡



*ዶ/ር ጌታቸው ቶሌራ*
*የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር*
የኢትዮጵያ ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

## የስልጠና ማኑዋሉ መግቢያ

### አጠቃላይ ዳራ

የኢትዮጵያ ህገመንግስት፣ ብሔራዊ ህጎችና ፖሊሲዎች በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት መድሎዎችን የማስወገድ ስምምነት (CEDAW)፣ የቤጂንግ የድርጊት መርሀግብር፣ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር፣ የህፃናት መብቶች ስምምነት/ኮንቬንሽን ከመሳሰሉት አለምአቀፍ የስርዓተ-ፆታ እኩልነት ህጋዊ ሰነዶች ጋርተደጋጋፊዎች ናቸው፡፡ የወንዶችና የሴቶች እንዲሁም የልጃገረዶችና የታዳጊ ወንዶች እኩልነት ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ማእከላዊ ምሶሶዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግም በስርዓተ-ፆታ እኩልነት መርህ ላይ ተመስርቶሀምሌ 1992ዓ.ም በስራ ላይ ውሏል፡፡ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የቤት ውስጥ ጥቃትንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለምሳሌ ያለእድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋና የሴት ልጅ ግርዛትን በወንጀል የሚያስጠይቁ አድርጓቸዋል፡፡

በስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የተለያዩ አይነቶች ያሉት ሲሆን አካላዊ ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃትና ስነ-ልቦናዊ ጥቃት ይገኙበታል፡፡ ይህም ሆኖ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አብዛኛዎቹ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች ሴቶችና ልጃገረዶች ናቸው፡፡ ባህልን፣ ማህበራዊ መደብንና የኤኮኖሚ ደረጃንሳይለይበማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ አብዛኞቹ ጥቃት ፈፃሚዎች የቅርብ ሰዎች/ወዳጆች መሆናቸውን የተካሄዱ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ወሲባዊ ጥቃት በማህበረሰቡ የተወገዘ ሲሆን የጥቃቱን ተጎጂዎች ደህንነትና በአጠቃላይም ማህበረሰቡን በእጅጉ የሚጎዳ ነው፡፡በሴቶችና በወንዶች አካላዊ፣ ወሲባዊና ስነ-ተዋልዷዊ፣ አእምሯዊና ባህሪያዊ ጤና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳርፋል፡፡ ጤናነክ ስጋቶችና የሚያስከትሏቸው አስከፊ ውጤቶች ጎልተው ከማይታዩ ባህሪያዊ ችግሮች፣ ምንም አካላዊ ጉዳት አለመታየትና ካለመገኘት ጀምሮ እስከ ስር የሰደደ የጤና ችግሮችና አልፎም ሞት ያደርሳሉ፡፡

የጤናው ሴክተር ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በተወሰኑ ሆስፒታሎች ውስጥ በስልታዊ አቀራረብ ለማስተናገድ መሞከሩን ታሪክ ያስረዳል፡፡ የአዲስ አበባው ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ወሲባዊ ጥቃቶችን በማከም ረገድ ቀዳሚ ነው፡፡ የካቲት 12 ሆስፒታል የህፃናት ጥቃትና ቸልተኝነት ሰለባ ለሆኑ ህፃናት ህክምና ክፍል ፕሮጀክትን በ1993 አ.ም የጀመረ ሲሆን ከበርካታ ዘርፎች የተውጣጡ ሙያተኞችን ማለትም የስነልቦና ሀኪሞችንና የህፃናት ጥቃት መርማሪ ፖሊሶችን ያሰባሰበ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታልስርዓተ-ፆታንመሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችን ማስተናገጃ ሁሉንአቀፍ ማእከል በ1996 አ.ም አቋቁሟል፡፡የዘርፈብዙ አቀራረብ ስልት በአጋሮች ድጋፍና በፍትህ ሚኒስቴር ሰብሳቢነት በ1999 አ.ም የተጀመረ ነበር፡፡

አራተኛው የጤና ዘርፍ ልማት መርሀ ግብር ለስርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ጅምሮችን በማጠናከርና በማስፋትም በሴቶችና በልጆች ላይ ለሚደርሰው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሚሰጠውን የጤና ምላሽ ሁሉን አቀፍና ዘርፈ ብዙ መሆን በሚያስችለው ደረጃ ላይ እንዲደርስ ጉልህ ጥረቶችን አድርጓል፡፡

የዚህ የስልጠና ማንዋል ተቀዳሚ አላማም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተለይም ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች በቂ የህክምና እንክብካቤ መስጠትና የወንጀል መረጃዎችን መሰብሰብ እንዲችሉ የህክምና ባለሙያዎችን እውቀትና ክህሎት ማሻሻል ነው፡፡የህክምና ባለሙያዎቻችን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ለማከም የሚሰጡትን ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች ብቻቸውን መስጠት የማይችሉ በመሆናቸው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና ለወሲባዊ ጥቃት ውጤታማ ምላሽ መስጠት ዘርፈ ብዙና የተሳለጠ አቀራረብ የሚጠይቅ ነው፡፡የጤና ሀላፊዎችን፣ የጤና ባለሙያዎችንና ማህበረሰቡን ማሰልጠን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች በሁሉም የጤና ተቋማት የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራት ለማስጠበቅና ማህበረሰቡ የሚሰጠውን እንክብካቤ ለማሻሻል ያግዛል፡፡

ይህ የስልጠና ማንዋል በአምስት ሞጁሎች የተዋቀረ ሲሆን የጤና ባለሙያዎች ጠቃሚ መረጃዎችን በቀላሉ እንዲያገኙ በማድረግ እውቀታቸውን፣ አቅማቸውንና ክህሎታቸውን ይበልጥ ያጠናክራሉ። በተጨማሪም እነዚህ የተለያዩ ሞጁሎች የተሳታፊዎችን ክህሎትና ግንዛቤ ለማሻሻል ብቃት ተኮር መርሆዎችን መሰረት አድርገው የተቀረፁ ናቸው።

## በሞጁሎች የተደገፈው የስልጠና ፓኬጅ ያስፈለገበት ምክንያት

አምስቱም የተሳታፊ ሞጁሎች በተለያዩ የጤና ባለሙያዎች ዘንድ አስፈላጊ ለሆኑ ክህሎቶችና እውቀቶች አፅንኦት የሰጡ ሲሆኑ ይህም በተጨባጭ የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን የመድፈን እድል ይሰጣሉ። ለምሳሌ ሞጁል ሁለት ሀኪሞች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጋቸውን ክህሎት የሚያጠናክር ሲሆን ሞጁል ሶስት ደግሞ የስነ-ልቦና ሀኪሞች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች የሚሰጡ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ስነ-ልቦናዊ ድጋፎችን በተመለከተ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ ያገለግላል። በተጨማሪም ሞጁል አራት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በተመለከተ ጤነኛ አመለካከት ለመፍጠርና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከያ ስልቶችን ለማሻሻል የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚጠቀሙበት መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።በአገልግሎት ጥራት ክትትል ወቅት የአቅምና የእውቀት ክፍተት ከተስተዋለም እነዚህን የተለያዩ ሞጁሎች በመጠቀም ባለሙያዎችን መልሶ በማሰልጠን አገልግሎቶቹን በላቀ ደረጃ መስጠት እንዲችሉ ማብቃት ይቻላል።

## ቁልፍ ክህሎቶች

እነዚህ ማንዋሎች የሚከተሉትን ቁልፍ ክህሎቶች ለተሳታፊዎች መስጠት በሚያስችል መልኩ የተቀረፁ ናቸው፡-

**ሞጁል 1፡** ይህ ሞጁል የስርዓተ ፆታ ፅንሰ-ሀሳቦች የቃላት ፍች፣ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና አይነቶች፣ የጥቃቱ የጉዳት መጠንና የሚያስከትለው ውጤት፣ ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ለመከላከል ባለብዙ ተቋማዊ ዘዴ ያለው ጠቀሜታ እና በኢትዮጵያ ያሉ ሀገራዊ ህጎችና ፖሊሲዎች እንዲሁም ኢትዮጵያ የተፈራረመቻቸው አለም አቀፍ የህፍ ስምምነቶችን በጥልቀት ይዳስሳል።

**ሞጁል 2፡**

- ❖ ***ግንዛቤ***

**ክፍል 2.1፡** ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አቀራረብ መርሆችን አጠቃቀም የተመለከተ እውቀት። የተከሰተውን ሁኔታ ጥቃቱ ለደረሰባቸውና ለቤተሰቦቻቸው ማስረዳት፣ የተዘውታሪ ቃላትን ፍቺ መረዳት።

**ክፍል 2.2፡** የመጀመሪያ የህክምና አቀራረብና የታካሚ አያያዝ ሂደትን የተመለከተ እውቀት፤የአካላዊ ምርመራና የላብራቶሪ ውጤቶችን ትርጉም መረዳት።

**ክፍል 2.3፡** የህክምና ክትትል አላማን፣ መርሀግብርንና ተግባራትን መግለፅ።

- ❖ ***ክህሎት***

**ክፍል 2.1፡** የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም፤ለጥቃት ተጎጂዎች በስነ-ምግባር የተሞላ ትክክለኛ የምክክር አገልግሎት አሰጣጥና አያያዝ፤የኤች.አይ.ቪ፣ የአባለዘር በሽታዎችና የሄፐታይተስ ቢ ምርመራና የምክክር አገልግሎት፤ የወንጀል መረጃዎች አሰባሰብ

**ክፍል 2.2፡** የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ ተፈላጊውን ህክምና የማዘዝ፣ ትክክለኛ የህክምና የምክክር አገልግሎት አሰጣጥንና ትክክለኛ የመረጃ አያያዝ

**ክፍል 2.3፡** በእያንዳንዱ የህክምና ክትትል ጉብኝት ወቅት ሁሉን አቀፍ እንክብካቤ የመስጠት ችሎታን በተግባር ማሳየት፣ የህክምና ቅብብሎሽ/ሪፈራል ማድረግ፣ ህግነክ የህክምና ሰነዶች/ሰርተፊኬት አዘገጃጀት

**ሞጁል 3፡**

- ***ግንዛቤ፡*** ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የሚያስከተላቸውን ዋነኛ ስነልቦናዊ ጉዳቶች ማብራራት፤ የተለያየ አይነትና ደረጃ ላላቸው ስነልቦናዊና ማህበራዊ ተግባራት አገልግሎት አሰጣጥ መረዳት
- ***ክህሎት፡*** ስርአተፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች የምክክር አገልግሎት መስጠት

**ሞጁል 4፡**

- ***ግንዛቤ፡*** ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት መከላከያ ቁልፍ መርሆችን መግለፅ፤ በስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ረገድ የጤና ባለሙያዎች ያላቸውን ሚና መግለፅ
- ***ክህሎት፡*** ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች በንቃት መለየት፤ በጤና ተቋም ውስጥ የሚካሄዱ የጤና ትምህርት ክፍለጊዜዎችን መምራት፤ የማህበረሰብ ንቅናቄና የማህበረሰብ ውይይት መምራት እንዲችሉ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን በመደገፍ ማብቃት

**ሞጁል 5፡**

- ***ግንዛቤ፡*** የድህረ-ወሲባዊ ጥቃት እንክብካቤ ክትትልና ምዘና አላማና ጠቀሜታ መግለፅ
- ***ክህሎት፡*** አመላካቾችን ተጠቅሞ ሪፖርት ማዘጋጀት፤ የድህረ-ወሲባዊ ጥቃት እንክብካቤ መመዝገቢያ ቅፅ መጠቀምና መሙላት

## የስልጠና ጊዜው ይዘት

**የስልጠና ጊዜው ሙሉ መግለጫ**

የዚህ አራት ቀናት የሚፈጅ የስልጠና ጊዜ እቅድ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን በመከላከል ዙሪያ የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎችንና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን እውቀትና ክህሎት ማሻሻል ነው፡፡

**የስልጠና ጊዜው አላማ**

የዚህ ስልጠና ጊዜ አላማ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችል የተሻለ እውቀትና ክህሎት ተሳታፊዎች እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡

***የተሳታፊዎች መማማሪያ አላማዎች***

ተሳታፊዎች ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ይጨብጣሉ፡-

<u>መግቢያ</u>

<u>ሞጁል 1</u>፡ ስርአተፆታ እና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መግቢያ

<u>ሞጁል 2</u>፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የጤናው ህክምናዊ ምላሽና አመራር

<u>ሞጁል 3</u>፡ ስነ-ልቦናዊ ክትትልና ማህበራዊ ስነልቦናዊ ድጋፍ

<u>ሞጁል 4</u>፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል

<u>ሞጁል 5</u>፡ ክትትልና ግምገማ

***የስልጠና/የመማማሪያ ዘዴዎች***

- በምሳሌ የተደገፉ ገለፃዎችና የቡድን ውይይቶች
- የግልና የቡድን መልመጃዎች
- የሚና ጨዋታዎችና ምሳሌያዊ ጥናቶች/ኬዝ ስተዲስ

- አሰልጣኞች ግብረመልስ የሚሰጡባቸው ህክምናዊ የተግባር ልምምዶችን አስመስሎ ክፍል ውስጥ መስራት

**የስልጠና/የመማማሪያ ቁሳቁሶች**

ይህ ስልጠና ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አብሮ እንዲሰጥ የተቀረፀ ነው፡-

- ብሔራዊ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ስልጠና ፓኬጅ፡-
  - የስልጠና ሞጁሎች ከ1-5
  - የአሰልጣኞች/የአመቻቾች መመሪያ
  - የትምህርት መስጫ ማቅረቢያ/ፓወርፖይንት ስላይዶች

- የኤች.አይ.ቪ ምክርና ደም ምርመራ፣ ሄፐታይተስ፣ የአባለዘር በሽታዎች ቁጥጥር፣ የቤተሰብ ምጣኔ ብሄራዊ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርአት ሰነድ (SOPs)

**የተሳታፊ መምረጫ መስፈርቶች**

በዚህ የስልጠና ጊዜ ተሳታፊ መሆን የሚገባቸው በጤና ተቋም ደረጃ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት፣ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ማለትም የስነተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት ጤና አግልግሎት በብቃት በመስጠት ላይ የሚገኙ ወይም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት አገልግሎቶችን የመስጠት ሀላፊነት ያለባቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የስነልቦና አማካሪዎች/ክሊኒካል ሳይኮሎጂስቶች ናቸው፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ባለሙያዎች የተጠቀሱትን አገልግሎቶች በሚሰጡባቸውና ሊጀመሩ በታቀዱባቸው አገልግሎት መስጫ ተቋማት ወይንም ይህንን አገልግሎት በሚቆጣጠር ተቋም ውስጥ በአሁን ወቅት በመስራት ላይ የሚገኙ መሆን አለባቸው፡፡

**አሰልጣኝ መምረጫ መስፈርቶች**

የዚህ ስልጠና አሰልጣኞች ዋና/ማስተር አሰልጣኞች ወይም የአሰልጣኞች ስልጠና የወሰዱ መሆን ይገባቸዋል፡፡

**የምዘና ዘዴዎች**

**ለተሳታፊ፡**

- ቅድመ-ስልጠና እና ድህረ-ስልጠና የእውቀት መመዘኛ
- የአፈፃፀም ደረጃ ማለትም በቡድን ስራዎች፣ በምሳሌያዊ ጥናቶች/ኬዝ ስተዲስ፣ በሚና ጨዋታዎች፣ ህክምናዊ የተግባር ልምምድ ላይ የሚደረግ ተሳትፎ

**ለስልጠና ሂደት፡**

- የስልጠና ምዘና (በእያንዳንዱ ተሳታፊ የሚሞላ)

**ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ፡** አምስት ቀናት - በግምት 4 ሰአታት የሚወስድ የክፍል ውስጥ ህክምናዊ የተግባር ልምምድ

**የስልጠና ቦታ፡** ስልጠናዎቹ የሚሰጡት በብሄራዊ የስራ ላይ ስልጠና ማእከላት ይሆናል

**የስልጠናው ተሳታፊዎች ስብጥር፡** ከ30 ያልበለጡ ተሳታፊዎችና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት/በወሲባዊ ጥቃት ላይ በሀገር ደረጃ የተረጋገጠ ብቃት ያላቸው ከ3-4 የሚደርሱ አሰልጣኞች፡፡

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ወገኖች የጤናው ሴክተር ምላሽ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

2009 ዓ.ም

## የተሳታፊ ማንዋል ፦ ሞጁል አንድ

# ስርአተፆታ እና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መግቢያ



# ሞጁል 1፡ የስርዓተ-ፆታ መሰረታውያን መግቢያና ዳራ

## ማውጫ

**መግቢያ** ..... **10**

**ክፍል 1፡ የስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብና ተዘውታሪ ቃላት** ..... **10**

1.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች ..... 10

1.2 የስርዓተ-ፆታ ፅንሰሀሳብ ..... 10

1.3 የተዘውታሪ ቃላት ፍቺዎች ..... 11

**ክፍል 2፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና የጥቃት አይነቶቹ** ..... **13**

2.1 የክፍለጊዜው አላማዎች ..... 13

2.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ..... 13

2.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነቶች ..... 15

**ክፍል 3፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠንና የሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች** ..... **19**

3.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች ..... 19

3.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠን ..... 19

3.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች ..... 19

**ክፍል 4፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዘርፈብዙ ምላሽ/አቀራረብ** ..... **21**

4.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች ..... 21

4.2 ዘርፈብዙ ምላሽ ..... 21

**ክፍል 5፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምላሽን በተመለከተ ህጋዊው አውድ እና የሙያ**

5.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች ..... 24

5.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መሰረት ያደረግ ያለው ህጋዊ አውድ ..... 24

5.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት የባለሙያዎች የሙያ ስነምግባር ..... 26

**የሞጁል 1 ማጠቃለያ** ..... **27**

**የተሳታፊዎች ግለ-ምዘና** ..... **27**

## መግቢያ

ይህ ሞጁል ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ፅንሰሀሳብ የጋራ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እግረመንገዱንም ለተከታይ የስልጠና ሞጁሎች መሰረት ይጥላል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ስርዓተ-ፆታን መሰረት ስላደረገ ጥቃት ፅንሰ ሀሳቦች ግንዛቤ የሚያጨብጥና የተዘውታሪ ቃላት ፍቺዎችን የሚሰጥ ነው፡፡ ክፍል ሁለት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ምንነትና መሰረታዊ የጥቃት አይነቶችን ያብራራል፡፡ ክፍል ሶስት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠንና የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች የሚያብራራ ሲሆን ክፍል አራት ደግሞ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዘርፈብዙ አቀራረብ ስላለው አስፈላጊነት ይዳስሳል፡፡ በስተመጨረሻም አምስተኛው ክፍል ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/የወሲባዊ ጥቃትን ህግነክ አውድ ከጤና አንፃር የሚዘረዝር ሲሆን ወሳኝ ብሄራዊ ህጎችንና ፖሊሲዎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን አለምአቀፍ የህግ ሰነዶች በአጭሩ ይዳስሳል፡፡

# ክፍል 1፡ የስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብና ተዘውታሪ ቃላት

## 1.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች

ይህ ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡-

- የስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብን ማብራራትና ከጤና ጋር ማዛመድ
- ስርዓተ-ፆታ ነክ ተዘውታሪ ቃላትን ማብራራት

**ቁልፍ ክህሎቶች**

- የስርአተፆታ መሰረታዊ ፅንሰሀሳብ እውቀት
- ስርአተፆታን የማብራራት ችሎታ
- ተዘውታሪ ቃላትን በአግባቡ መጠቀም

## 1.2 የስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብ

**ስርዓተ-ፆታ** ማለት የማህበረሰብ አመለካከት የፈጠረውና በማህበራዊ ግንኙነት ሂደት ውስጥ ያሉትን የወንዶችንና የሴቶችን ልማዳዊ ደንቦች፣ ሚናዎችና ግንኙነቶች የሚወስን ነው፡፡ **ስርዓተ-ፆታ** ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ልጃገረዶችና ታዳጊ ወንዶች በማህበረሰቡ ውስጥ ምን አይነት ባህሪያትን ማሳየትና እንዴት ተግባራትን መፈፀም እንዳለባቸው ይወስናል፡፡

*ፆታ* ማለት የወንዶችና የሴቶች ስነ ህይወታዊ ልዩነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ *ፆታ* የወንዶችና የሴቶች አካላዊና ተፈጥሯዊ ልዩነት ሲሆን ወንድ ወይም ሴት የመሆንን መገለጫ የሚወስንልን ነው፡፡ ይህ ልዩነት የማህበረሰባዊ ልማዳዊ ደንቦች ተፅእኖ የሚያርፍበት ሲሆን በወንዶችና በሴቶች አጠቃላይ እድገት ውስጥ የሚኖሩትን የተለያዩ እድሎችና ተሳትፎዎችን ይመራል፡፡

የጤና ፅንሰሀሳብ ስነ-ህይወታዊ አይነተኛ ጠባያት ከስርዓተ-ፆታ (ማህበራዊ ወሳኞች) ጋር መስተጋብር የሚፈጥሩበትን የሰው ልጅ ውስብስብ ሁኔታ ያካትታል፡፡ ይህ ደግሞ በፊናው የበሽታ አካሄድ ሁኔታ፣ ስጋቶች፣ ህክምናና ውጤቶች ላይ ተፅእኖ ያሳርፋል፡፡

**መልመጃ 1.1**

*የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አንብቡና በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ "ስርዓተ-ፆታ" ወይም "ፆታ" በማለት መልሱ። መልመጃውን ለማጠናቀቅ ሶስት ደቂቃዎች አሏችሁ። አስከትሎም አመቻቹ መልሶቹን ያብራሩላችኋል።*

1. ሴቶች ልጅ ይወልዳሉ፤ ወንዶች ግን አይወልዱም ________
2. በኢትዮጵያ አብዛኞቹ የቀዶ ህክምና ሀኪሞች ወንዶች ናቸው ________
3. የልብ ህመም ከሴቶች ይልቅ በወንዶች ላይ በይበልጥ ይከሰታል ________
4. ሴቶች ከወንዶች በበለጠ በአንገት ቦይ ካንሰር ይጠቃሉ ________
5. በደቡብ ክልል ወንዶች በቤት ውስጥ የሽመና ስራ ይሰማራሉ ________
6. ሴቶች ከወንዶች በበለጠ በኤች.አይ.ቪ. የመያዝ እድል አላቸው ________
7. ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው በርካታ ሴቶች የህክምና አገልግሎት አይፈልጉም ________
8. የቲቢ በሽታ በወንዶች ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ የመዳን እድል ያለው ሲሆን በሴቶች ላይ ደግሞ በከፍተኛ መጠን ይከሰታል ________

## 1.3 የተዘውታሪ ቃላት ፍቺዎች

ስለስርዓተ-ፆታ ስንገልፅ አዘውትረን የምንጠቀማቸውን የተወሰኑ ቃላት ማወቅና በተመሳሳይ መልኩ መረዳት ያስፈልጋል። የስርዓተ-ፆታ ነክ ቃላትንና በስርዓተ-ፆታ መሰረት ያደረገ ፆታዊነት ላይ ያላቸውን ተፅእኖዎች መረዳት ከወሲባዊ ጥቃት የፀዳ ማህበረሰብን ለመፍጠር ያግዛል።

*ቀጥሎ የተወሰኑ ተዘውታሪ ቃላት ከነፍቻቸው ቀርበዋል፦*

- **የስርዓተ-ፆታ ልማዶች/Gender norms፤** ማለት ማህበረሰባዊ "ህጎች" ወይም "ደንቦች" (የማህበረሰባዊ ባህል ደንቦች ይዘት ያለው) ስብስብ የሚጠቁም ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ባህርያት ወንዶችና ሴቶች በምን መልኩ ማሳየት፣መከተል ወይም መተግበር እንዳለባቸው ያበረታታል። ይህም "የድግግሞሽን ሂደት" የሚያሳይ ሲሆን ግለሰቦች እንደ ቡድን አባልነታቸው ወይም የአንድን ማህበረሰብ ይዞታ በመወከል እንደየሁኔታው ማድረግ የሚገባቸውንና ከእነሱም የሚጠበቅባቸውን ነገሮች ይገልፃል።ልማዳዊ ደንብ ይህንን አላማ ማሳካት ይችል ዘንድ የማህበራዊ የቁጥጥር ስርአትን መወከል የሚገባው ሲሆን መገለጫውም በጅምላ የመፈረጅ (በተለያዩ አውዶች መተግበር የሚችሉ - ቁንጽል መመሪያ ሳይሆን እንደ"መርህ" የሚተገበር ነው) እንዲሁም ሆን ተብሎ (አንድ ልማዳዊ ደንብ የተቆጣጣሪነት ሚናውን ለማሳካት የሚተገበር ድርጊት ነው) ስለሆነም ልማዳዊ ደንቡን እንደ ስርዓት በመቀበል የሚገባ ሲሆን ካልሆነ ግን በህብረተሰቡ ዘንድ ዋጋ ያስከፍላል።
- **ስርዓተ-ፆታዊ ሚናዎች/Gender roles፤** ማለት ማህበራዊ ሚና ሲሆን ሴቶችና ወንዶች መስራት አለባቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ተግባራት ስብስብ ያመለክታል፡
ማህበራዊ ሚናዎች ሁልጊዜም ቢሆን ከፈጠራቸው ማህበረሰብ የእሴት ስርአት ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው። እነዚህ ሚናዎች "ከማህበረሰቡ የተሰጡ" ባህሪያትና ድርጊቶች ናቸው። ስለዚህ "ግለሰቦች በተጨባጭ የሚተገብሯቸው ሚናዎች በሚታሰበው ሚና ምክንያት ሊለያዩ ይችላሉ፤ የሚፈለግ ባህሪይ (የሚናው ባለቤት የግድ የምትፈፅመው ወይም የሚፈፅመው)፣ ተፈላጊ ባህሪይ (የሚናው ባለቤት መፈፀም የሚኖርባት ወይም የሚኖርበት)፣ ቅቡል ባህሪይ (የሚናው ባለቤት እንደቻለው የምትፈፅመው ወይም የሚፈፅመው) እና ተቀባይነት የሌለው ባህርይ (የሚናው ባለቤት ላይኖረውና ወይም ላይኖራት የሚችል። ስለዚህም የማህበራዊ ሚናዎች አተገባበር እንደ አስፈላጊነቱ የሚለዋወጥ ሲሆን ነገር ግን ለማህበራዊ ቁጥጥርና አልፎ አልፎም ለማህበራዊ ቅጣት ክፍት ነው።"

- **ስርዓተ-ፆታዊ ግንኙነቶች/Gender relations**፤ ይህ የሚያመለክተው በስርዓተ-ፆታ ልማዶችና ሚናዎች ላይ ተመስርተው በሴቶችና ወንዶች መካከል የሚኖሩ ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚገልፅ ነው፡፡

- **ስርዓተ-ፆታዊ ፍረጃዎች/ድምዳሜዎች/Gender stereotypes**፤ ስርዓተ-ፆታዊ ፍረጃዎች/ድምዳሜዎች በህልው አእምሮ ውስጥ ተደላድሎ የሚገኝ ሲሆን ይኸውም በአስተያየት፣ በብያኔ፣ በአመለካከትና በባህሪይ ላይ ተፅእኖ በማሳረፍ አመለካከትን የሚገሩና አንድን ክስተት የሚመዝኑ ስነልቦናዊና ማህበራዊ አሰራሮች ናቸው፡፡ ፍረጃን/ድምዳሜን በተመለከተ የተወሰኑ አይነተኛ ጠባያትን ለሁሉም ሰው መገለጫ አድርጎ በአንድነት/በጅምላ የማካተት ልምድ ነው፡፡ ፍረጃ/ድምዳሜ የስሜታዊነት፣ የመሰረተቢስነትና አንድን ክስተት አቅልሎ የመተርጎም ባህሪያት ያሉት ሲሆን በዚህም የተነሳ ለፕሮፓጋንዳ አላማ ይውላል፡፡
  ተባእትነትና አንስትነት በማህበረሰብ ዘንድ እኩል አይታዩም፡፡ ከፍረጃዊ/ከድምዳሜያዊ የተባእትነትና እንስትነት አመለካከት ውጪ አንዱን ፆታ ከሌላው ለይቶ ማንኳሰስ (አብዛኛውን ጊዜ ሴቶችን) ወይም ተቀባይነት መንሳት ፆታዊ ትምክህተኝነት ይባላል፡፡ ፆታዊ ትምክህተኝነት ልክ እንደዘረኛነት ያለመቻቻል መገለጫ ነው፡፡ ዘረኛነት በጎሳ ወይም በብሄር ላይ ተመስርቶ ሰዎችን ማንኳሰስ ሲሆን ፆታዊ ትምክህተኝነት ደግሞ በፆታ ላይ ተመስርቶ ሰዎችን ማንኳሰስ ነው፡፡

- **ስርዓተ-ፆታዊ ፍትሀዊነት/Gender equity**፡- በፆታ ላይ የተመሰረተ ማንኛውም አይነት አድልዎ ሳያደርጉ ለምሳሌ የሀብት ምደባን፣ ፕሮግራሞችንና የውሳኔ ሰጪነት ስልጣንን ለወንዶችና ለሴቶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የመደልደል ሂደት ሲሆን ይህ ደግሞ በተመሳሳይ ጊዜ ፍላጎታቸውን መሰረት አድርጎ ለወንዶችና ለሴቶች የቀረቡ ጥቅማጥቅሞችን በተመለከተ ያለውን ማንኛውም አይነት አለመመጣጠን እያስተካከሉ መሄድን ያካትታል፡፡

- **ስርዓተ-ፆታዊ እኩልነት/Gender equality፡-** *የሴቶችንና የወንዶችን እንዲሁም የልጃገረዶችንና የታዳጊ ወንዶችን እኩል መብቶች፣ ሀላፊነቶችና ምቹ እድሎች* የሚገልፅ ነው፡፡ ስርዓተ-ፆታዊ እኩልነት የሁለቱን ቡድኖች ልዩነት በመገንዘብ ለወንዶችና ለሴቶች ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ከግንዛቤ መግባታቸውን ያመለክታል፡፡ ስርዓተ-ፆታዊ እኩልነት የሚሳካው በሁሉም ማህበራዊ መስኮች ወንዶችና ሴቶች እኩል መብቶችንና ምቹ እድሎችን ማጣጣም ሲችሉ ነው፡፡ ይኸውም ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎንና ውሳኔ ሰጪነትን የሚያካትት ሲሆን የወንዶችና የሴቶች ባህሪያት፣ ምኞቶችና ፍላጎቶች እኩል ዋጋ እና ተቀባይነት የሚያገኙበት ነው፡፡

- **ስርዓተ-ፆታዊ ማብቃት/Gender empowerment**፡- ማብቃት ዘርፈ-ብዙ ማህበራዊ ሂደት ሲሆን ሰዎች በህይወታቸው ላይ ስልጣንና የቁጥጥር አቅም እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው፡፡ ግንዛቤን ማሳደግ፣ በራስመተማመንን መገንባት፣ ምርጫዎችን ማስፋትና የሀብት ተደራሽነትና ባለቤትነት ማሳደግና ስርዓተ-ፆታዊ አድልዎንና የእኩልነት መዛባትን የሚያጠናክሩና የሚያስቀጥሉ መዋቅሮችንና ተቋማትን የመቀየር እርምጃዎችን ያካትታል፡፡ መብቃት ማለት የእኩል ብቃቶች ባለቤትነት (ለምሳሌ የትምህርትና የጤና) እና የሀብትና ምቹ እድሎች በእኩል ተደራሽነት (ለምሳሌ የመሬትና የስራ እድል) ብቻ ሳይሆን ግለሰቡ ስልታዊ ምርጫዎችንና ውሳኔዎችን እንዲወስድ (ለምሳሌ በአመራር ቦታ እድሎችና በፖለቲካ ተቋማት ተሳትፎ በኩል የሚሰጡ) እነዚህን ብቃቶች፣ መብቶችና እድሎች መጠቀም የሚችልባቸው መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፡፡

- **ስርዓተ-ፆታን ማካተት/Gender mainstreaming**፤ በማንኛውም ዘርፍና ደረጃ የትኛውም አይነት የታቀደ ተግባር፣ ህግ፣ ፖሊሲ ወይም ፕሮግራም በሴቶችና በወንዶች ላይ የሚኖረውን አንድምታ የመገምገም ሂደት ነው፡፡ በሁሉም ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎችና መርሀ-ግብሮች ቀረፃ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ምዘና በሚካሄድበት ወቅት የወንዶችንና የሴቶችን ፍላጎቶችና ተሞክሮዎች ማእከላዊ ማጠንጠኛ የሚያደርግ እስትራቴጂ ሲሆን ወንዶችና ሴቶች እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትና የእኩልነት መዛባት የሚቀረፍበት ስልት ነው፡፡ የመጨረሻ ግቡም ስርአተፆታዊ እኩልነትን ማስፈን ነው፡፡

**መልመጃ 1.2 ካርድ ማዛመድ**

*አሰልጣኙ/አመቻቹ አስቀድመው የተዘጋጁ አባባሎችን በፍሊፕ ቻርት ላይ ከፃፉ በኋላ በግድግዳ ላይ ይለጥፋሉ። ከስርአተፆታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላት ከተፃፉባቸው በርካታ ካርዶች ውስጥ ያገኛችሁትን እንድታነሱና በፍሊፕ ቻርት ላይ ከተፃፈው አባባል ጋር እንድታዛምዱ ትጠየቃላችሁ። ይህንን ተግባር ለማጠናቀቅ 10 ደቂቃዎች ያህል የሚወስድ ሲሆን ንቁ ተሳትፏችሁ በጣም አስፈላጊ ነው።*

# ክፍል 2፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና የጥቃቱ አይነቶች

## 2.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች

ይህ ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ፡-

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ፍቺ/ምንነትን ማሳወቅ
- ዋና ዋና የተለመዱ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥቃት አይነቶችን ማብራራት

**ቁልፍ ክህሎቶች፡**

*ግንዛቤ፤*

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ትርጉምና አይነቶቹን የተመለከተ እውቀት

## 2.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን በተመለከተ የተለያዩና ነገር ግን ተመሳሳይነት ያላቸው ፍቺዎች/ትርጉሞች አሉ።

**ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት** አብዛኛውን ጊዜ ሴቷ ተጎጂ በምትሆንባቸው ሴቶችና ወንዶች የተሳተፉባቸውን የጥቃት አይነቶች በሙሉ የሚያካትት ነው። "በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረተ" የሚለው ቃል ሴቶችና ልጃገረዶች በማህበረሰብ ውስጥ ባላቸው የበታችነት ደረጃ አውድ ውስጥ ያለውን ጥቃት መረዳት አስፈላጊ መሆኑን ለማጉላት ነው። ይህንን አይነቱን ጥቃት በሴቶች የጥቃት ተጋላጭነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ካላቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ልማዳዊ ደንቦች፣ ማህበራዊ መዋቅሮችና ስርአተፆታዊ ሚናዎች ነጥሎ መረዳት ፈፅሞ አይቻልም።

**የቤት ውስጥ ጥቃት፡-** በርካታ ትርጉሞች እየተሰጡት አገልግሎት ላይ የሚውል ቃል ነው። በስፋት የተለመደው አጠቃቀሙ በእጮኛ ወይም በቅርብ አጋር የሚፈፀመውን ጥቃት ለመግለፅ ነው። ይህም ሆኖ ቃሉ በቤተሰብ ውስጥ የሚፈፀመውንና አብዛኛውን ጊዜም ጥቃት ፈፃሚዎቹ ወንዶች የቤተሰብ አባላት የሆኑበትን ጥቃት ለመግለፅም ይውላል። ለምሳሌ አባት በሴት ልጁ ላይ፣ ወንድ ልጅ በእናቱ ላይ ወዘተ የሚፈፅሚቸው ጥቃቶች።

*"ማንኛውም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶች ላይ የሚደርስ የአካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ወይም ስቃይ ውጤት ሲሆን በጋራ ወይም በግል ህይወት ላይ ሊያደርስ የሚችል ማንኛውም አይነት ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ማስገደድ ወይም ጭፍን የነፃነት ገፈፋን ይጨምራል"* (የተባበሩት መንግስታት አጠቃላይ ጉባኤ፣ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ማስወገጃ አዋጅ፣ እ.ኤ.አ 1993)

**በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት፡-** ብዙ ጊዜ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ካደረገ ጥቃት ጋር በተመሳሳይነት የሚያገለግል ቃል ነው። ነገር ግን ቃሉ ጥቃቱ የመነጨው በማህበረሰብ ውስጥ ባለው

የሴቶችና ወንዶች ግንኙነት ውስጥ እኩልነት ከጎደላቸው የሃይል ግንኙነቶች መዛባት/አለመመጣጠን መሆን አለመሆኑን በግልፅ አያስቀምጥም፡፡

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚከሰተው በግንኙነቶች መካከል ከሚገኝ የሀይል አለመመጣጠን የተነሳ ነው፤ ለምሳሌ አካላዊ (ጡንቸኝነት/ጥንካሬ፣ መጠን፣ የጦር መሳሪያ መጠቀም፣ ተደራሽነትን ወይም ደህንነትን መቆጣጠር)፤ እድሜ (አብዛኛውን ጊዜ ታዳጊዎችና አዛውንቶች ተጋላጫ ናቸው)፤ ኢኮኖሚያዊ (ገንዘብ ላይ ማዘዝ ወይም የእቃዎች/የአገልግሎቶች/የአድልዎ ተጠቃሚነት)፤ ማህበራዊ (የአቻ ግፊት፣ ማስፈራራት፣ መሪ፣ መምህር፣ ወላጆች)፤ ፖለቲካዊ (ተመራጭ መሪዎች፣ ባለስልጣናት፣ አድሏዊ ህጎች)፡፡

ጥቃት ፈፃሚዎቹ (አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች) ከላይ ከተጠቀሱት የሀይል ግንኙነቶች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዛም ከፍ ባለው "ተጨባጭ" ወይም "ታሳቢ" ሀይል አላቸው፡፡ ሀይል ከምርጫ ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነው፡፡ አንድ ሰው የበለጠ ሀይል ሲኖረው ምርጫዎቹም የዛኑ ያህል ይሰፋሉ፤ በተገላቢጦሹም እንደዛው፡፡ አነስተኛ ሀይል ያላቸው ሰዎች የሚኖራቸው ምርጫ ጥቂት በመሆኑ ለጥቃት ተጋላጭ ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሀይልን አላግባብ መጠቀምን ያካትታል፡፡

ጥቃት ማለት ሀይልን/ስልጣንን መጠቀም ማለት ነው፡፡ "ሀይል" በባህሪይው አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሀይል ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ማሳደድ ወይም ሌላ አይነት ስነልቦናዊ ወይም ማህበራዊ ጫናዎችን ያካትታል፡፡ የጥቃቱ ኢላማ የሚሆነው ሰውም የሚደርሱበትን ተጨባጭና ጎጂ ጦሶች በመፍራት ወይም ቃል የተገቡለትን ጥቅሞች በማሰብ የሚጠበቅበትን ወይም የተጠየቀውን ለመፈፀም ይገደዳል፡፡ ጥቃት መፈፀም (መብቶችን መጣስ) አንድን ሰው ከፍላጎቷ/ቱ በተፃራሪ ወይም ከ"ፈቃድ" ውጪ አንድን ድርጊት እንድትፈፅም/እንዲፈፅም ማድረግ ማስገደድ ማለት ነው፡፡

"ፈቃድ" ማለት በሆነ ነገር ላይ መስማማት ወይም ማፅደቅ፤ በእኩል የሀይል ግንኙነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች በግልፅ በቀረቡ "ምርጫዎች" ላይ በነፃነትና በውጤታ ውሳኔዎችን መስጠት ማለት ነው፡፡ የጥቃት ተግባር አንድ ሰው ያለውን የውሳኔ ሰጪነት መብት ይሽራል ወይም የቀረበለትን ግዴታ እንዲፈፅም ያስገድደዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህፃናት (ከ18 አመት በታች) ከወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው እውቅና ውጪ ማንኛውንም አይነት የስምምነት ፈቃድ ለመስጠት በህግ ይከለከላሉ፡፡

### መልመጃ 1.3 እውነት ወይም ሀሰት

*ለሚከተሉት ጥያቄዎች በተሰጠው ክፍት ቦታ እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡*
*መልመጃውን ለመጨረስ በግል 4 ደቂቃዎች አሏችሁ፡፡ ኋላ ላይ አሰልጣኙ/አመቻቹ ትክክለኛዎቹን መልሶች ያሳውቋቹኋል፡፡*

1. __________ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የወሲባዊ ጥቃት አካል ነው፡፡
2. __________ የቤት ውስጥ ጥቃት በቤተሰብ ውስጥ የሚከሰት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው፡፡
3. __________ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶችና በልጃገረዶች እና በወንዶችና በታዳጊ ወንዶች ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡
4. __________ አዋቂ ሰዎች ወሲባዊ ድርጊት ለመፈፀም ቢስማሙና በድርጊቱ ወቅት ግን ከልክ በላይ ሀይል የመጠቀም ሁኔታ ቢከሰት ድርጊቱ በክስ ወቅት ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተደርጎ ላይወሰድ ይችላል፡፡
5. __________ በህፃናት ላይ የሚፈፀም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ህገወጥ የሚሆነው አካላዊ፣ ወሲባዊ ወይም ስነልቦናዊ ጉዳት ወይም ስቃይ ካስከተለ ብቻ ነው፡፡
6. __________ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚከሰተው አብዛኛውን ጊዜ ለወንዶች ከሚያደላ የሀይል አለመመጣጠን የተነሳ ነው፡፡
7. __________ ጥቃት እኩልነት በጎደለው የሀይል ድልድል ላይ የተመሰረተ አቅምን መጠቀም ሲሆን በአንድ ግለሰብ ነፃና ውጤታዊ ውሳኔ ሰጪነት ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ ተግባራትን ያካትታል፡፡

## 2.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነቶች

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተለያዩ ቅርፆች የሚከሰት ሲሆን ረቂቅ እና ተጎጂን ለሞት እስከመዳረግ የሚደርሱ ጉልህ ድርጊቶችንም ሊያካትት ይችላል፡፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን በርካታ አይነቶች በዝርዝር ከማየታችን በፊት የጠራ አመለካከት እንዲኖረን የተወሰኑ ተያያዥ ቃላትን መረዳቱ አስፈላጊ ነው፡፡

**ጥቃት የደረሰባቸው/ሰለባዎች**

"ጥቃት የደረሰባት/በት" ወይም "ሰለባ" የሚሉትን ቃላት በተለዋዋጭነት መጠቀም ይቻላል፡፡ ሁለቱም ክስተቱ የተፈፀመበትን ወይም ኢላማ የሆነውን አካል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ "ሰለባ" የሚለው ቃል ከአንድ ክስተት የተረፉ እና/ወይም በክስተቱ የሞቱ ሰዎችን ለመግለፅ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ነገር ግን ከጤና አንፃር በምንነጋገርበት ወቅት "ጥቃት የደረሰባት/በት" የሚለውን ቃል መጠቀሙ ይመረጣል፤ በህይወት ያለን ሰው የሚመለከት ነውና፡፡ ከዚህም በላይ "ሰለባ" የሚለው ቃል ደካማ፣ ህመምተኛ፣ ትንሽ፣ ጎባጣ፣ አልቃሻ፣ ድሪቷምና በዚህ አለም ላይ ሰርቶ መኖር የተሳነውን ሰው ምስል በአእምሮ ላይ የሚፈጥር ነው፡፡ ይህ አሳዛኝና ወኔ ሰላቢ ቃል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ "ጥቃት የደረሰባት/በት" የሚለው ቃል ቀጥ ብሎ የቆመና ረጅም፣ አይን ለአይን የሚተያይ፣ በልበ ሙሉነት የሚራመድ፣ ህይወትን ጥግ ድረስ የሚያጣጥም ሰው ምስል በአእምሮ ላይ ይፈጥራል፡፡ ይህ ቃል የሀይል ሙላት ያለበት ብርታት አጎናፃፊ ቃል ነው፡፡

ጥቃት የደረሰባቸው/ተጎጂዎች የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

- ህፃናት፣ በተለይም ከወላጅ የተነጠሉ፣ ማደጎዎች
- ሴቶች፤ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ እንደ ሁለተኛ የህብረተሰብ ክፍል የበታች ተደርገው ስለሚቆጠሩ
- የወንድ ጥበቃ የሌላቸው ብቸኛ ሴቶች
- ያላገቡ ሴቶች፤ ሴት የቤተሰብ መሪ
- አእምሯዊ ወይም አካላዊ ጉድለት ያለባቸው ሴቶችና ወንዶች
- ኢኮኖሚያዊ ችግር ያለባቸው ሰዎች
- ወንድና ሴት አዲስ ስራ ተቀጣሪዎች፣ ተማሪዎች፣ ልዩ ጥቅም ያልተመቻቸላቸው የማህበረሰብ አባላት
- አናሳ የህብረተሰብ ክፍሎች ለምሳሌ ከጎሳ ወይም ከሀይማኖት አንፃር
- ጥገኝነት ፈላጊዎች፣ ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተፈናቀሉ

**ጥቃት ፈፃሚ**

***ጥቃት ፈፃሚ ማለት የጥቃት*** ተግባር/ሮችን የፈፀመ ወይም የተገበረ ሰው ማለት ነው፡፡ ጥቃት ፈፃሚው አካል በሌላ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ጥቃት ወይም ሌላ አይነት በደል የፈፀመ፣ የደገፈ ወይም የፈቀደ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ተቋም ሊሆን ይችላል፡፡

*ከጥቃት ፈፃሚዎች አይነተኛ ጠባያት መካከል፡-*

- ተጨባጭ ወይም ታሳቢ ሀይል ያላቸው ሰዎች
- በውሳኔ ሰጪነት ቦታ ላይ ያሉ ሰዎች
- ስልጣን ያላቸው ሰዎች

*ጥቃት ሊፈፅሙ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ዝርዝር ብዙ ቢሆንም ዋነኞቹ ግን የሚከተሉት ናቸው፡-*

- የቅርብ አጋሮች (ባሎች፣ ወንድ የፍቅር ጓደኞች)
- ተፅእኖ አሳዳሪ የህብረተሰብ ክፍሎች (መምህራን፣ መሪዎች፣ ፖለቲከኞች)
- የደህንነት ሀይሎች፣ ወታደሮች፣ ሰላም አስከባሪዎች
- ሰብአዊ እርዳታ ሰጪ ሰራተኞች (አለምአቀፍ፣ ዜጎች፣ ስደተኛ ተቀጣሪዎች)
- እንግዶች
- የማህበረሰብ አባላት
- ዘመዶች (ወንድሞች፣ አጎቶች፣ ወላጆች፣ አክስቶች እህቶች)
- ስልጣን ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው

በእያንዳንዱ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ውስጥ ጥቃቱ የደረሰበት ተጠቂና ጥቃቱን ፈፃሚ ሰው አለ። ስለዚህም ሁሉም በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ላይ ያተኮሩ እርምጃዎቻችን በጥቃት ፈፃሚና ጥቃት በደረሰባት/በት ላይ ያነጣጠሩ ሊሆኑ ይገባል።

**ሰብአዊ መብቶች፡**

ሰብአዊ መብቶች አለምአቀፋዊ፣ የማይገፈፉ፣ የማይነጣጠል፣ የተሳሰሩና የተደጋገፉ ናቸው።

- እያንዳንዱ ሰው ምንም አይነት የዘር፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም የሌላ አመለካከት፣ የሀገራዊ ወይም ማህበራዊ ምንጭ፣ የንብረት፣ የትውልድ ወይም የሌላ አይነት ቁመና ልዩነት ሳይደረግበት ሁሉንም መብቶችና ነፃነቶች እንዲጠቀም ተሰጥቶታል።
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መከላከልና ለጥቃቱ ምላሽ መስጠት ከሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው።
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ድርጊቶች በአለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ላይ የሰፈሩ የተለያዩ ሰብአዊ መብት መርሆችን ይጥሳሉ። ከበርካቶቹ መርሆች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-
  - *ማንኛውም ሰው በህይወት የመኖር፣ የነፃነትና የአካል ደህንነት መብት አለው*
  - *ማንኛውም ሰው በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ አካላዊና አእምሯዊ ጤና አጠባበቅ መብት አለው*
  - *ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ወይም አረመኔያዊ ከሆነ፣ ኢሰብአዊ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው*
  - *ማንኛውም ሰው የፈለገውን አመለካከት የመያዝና ሀሳቡን የመግለፅ፣ የመማር፣ የማህበራዊ ደህንነት፣ ራሱን የማሳደግ መብት አለው*

❖ **ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነቶች**

1. **አካላዊ ጥቃት** ማለት ሞት፣ አካለ ጎዶሎነት፣ ቁስለት ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ***ሆን ተብሎ*** የተወሰደ አካላዊ የሀይል እርምጃ ነው።

አካላዊ ጥቃት በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚያካትታቸው ነገሮች፤ መቧጨር፣ መግፋት፣ መላጨት፣ መወርወር፣ መጎተት፣ መመንተፍ፣ መንከስ፣ ማነቅ፣ መነቅነቅ፣ መወጋጋት፣ ፀጉር መጎተት፣ በጥፊ መምታት፣ መቆንጠጥ፣ ማቃጠል፣ ጦር መሳሪያ መጠቀም (ጠመንጃ፣ ቢላዋ ወይም ሌላ ቁስ)፣ መጠፈር፣ ወይም አካልን፣ መጠንን ወይም ጉልበትን በሌላ ሰው ላይ መጠቀም ጭምር ነው። በተጨማሪም አካላዊ ጥቃት ከላይ የተጠቀሱትን ድርጊቶች እንዲፈፅሙ ሌሎች ሰዎችን ማስገደድን ያካትታል። ከዚህም ሌላ አካላዊ ጥቃት አብዛኛውን ጊዜ በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ የማስመሰል ወይም የመተው ወይም የክልከላ/የቸልተኝነት/የማግለል ድርጊቶችን ያካትታል።

2. **ወሲባዊ ጥቃት/ብዝበዛ** ማለት የፈቃደኝነት ስምምነት በሌለበት እና/ወይም የፈቃደኝነት ስምምነት መስጠት በማይችል ለምሳሌ በህፃናትና በአካልጉዳተኞች ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ድርጊት ነው፡፡

ይህ ድርጊት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

(1) ድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ተፈፀመም አልተፈፀመ አካላዊ ጉልበት በመጠቀም አንድን ሰው ካለስምምነቱ በወሲባዊ ድርጊት እንዲሳተፍ ማስገደድ፡፡ ትንኮሳ፣ አስገድዶ መድፈር፣ በትዳር አጋር ተገድዶ መደፈር፣ ብዝበዛ፣ የህፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ/ከስጋ ዘመድ ጋር ወሲብ መፈፀም፣ ወሲባዊ ብዝበዛ (ብልት መጠቀም ያልተካተተበት)፣ ተገደው በወሲብ ንግድ መሰማራት ("ፈቅደው" ግን ደግሞ ሳይፈልጉ)፣ ህፃናትን በወሲብ ንግድ ማሰማራት፣ ወሲባዊ በሰዎች መነገድና ግዴታዊ ፅንስ ማቋረጥ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

(2) አንድ ግለሰብ የድርጊቱን ባህሪይ ወይም ሁኔታ ባልተረዳበትና በድርጊቱ ከመሳተፍ ራሱን ማቀብ ወይም ፈቃደኛ አለመሆኑን ለመግለፅ ባልቻለበት ሁኔታ ውስጥ (ለምሳሌ በህመም፣ በአካልጉዳተኝነት ወይም በአልኮል ወይም በሌላ አደገኛ ዕፅ ተፅእኖ ውስጥ ሆኖ፣ ወይም በማስፈራራት ወይም ጫና በማሳደር ምክንያት) ሙሉ በሙሉ የተፈፀመ ወይም የተሞከረ ወሲባዊ ድርጊት፡፡

(3) አዋቂ ሰው ወይም ከህፃኑ በእድሜ የሚበልጥ ሰው በህፃን ላይ የፈፀመው ማንኛውም ወሲባዊ ተግባር፤ የህፃኑን ወሲባዊ አካላት ከመደባበስ ጀምሮ በተግባር እስከተፈፀመ ወይም ለመፈፀም እስከተሞከረ ወሲባዊ ድርጊት ያሉትን ያካትታል፡፡

(4) *አስገድዶ መድፈር/አስገድዶ የመድፈር ሙከራ* ካለፈቃድ የሚፈፀም ወሲባዊ ግንኙነት ነው፡፡ በየትኛውም የአካል ክፍል ላይ የወሲብ ብልትን መጠቀም እና/ወይም በወሲብ ብልት ወይም በፊንጢጣ ላይ ቁስ ወይም የአካል ክፍል መጠቀምን ያካትታል፡፡ አስገድዶ መድፈር እና አስገድዶ የመድፈር ሙከራ ሀይል፣ ሀይል የመጠቀም ዛቻ፣ እና/ወይም ማስገደድ አለበት፡፡ ማንኛውም አይነት አካል የመዝለቅ ተግባር አስገድዶ መድፈር ነው፡፡ አካል መዝለቅን ያላስከተሉ አስገድዶ የመድፈር ጥረቶች አስገድዶ የመድፈር ሙከራ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

ሴቶችንና ወንዶችን አስገድዶ መድፈር አብዛኛውን ጊዜ ልክ እንደ አንድ ጠላትን ማጥቂያ ስልት በጦር መሳሪያነት የሚያገለግል ሲሆን ይኸውም ለድል አድራጊነት ምልክትነትና ሴቶችን ወይም የተማረኩ ተዋጊ ወንዶችን ለማዋረድ ይውላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለምሳሌ በይፋ የሚካሄድ ዝሙትንና ስካርን በሚከለክሉ አካባቢዎች ማህበራዊ ወይም ስነምግባራዊ ደንቦችን የጣሱ ሴቶችን ለመቅጣት ሊውል ይችላል፡፡ ሴቶችና ወንዶች በፖሊስ ጥበቃ ስር ሆነው ወይም በእስር ቤት ውስጥ ተገደው ሊደፈሩ ይችላሉ፡፡

አስገድዶ መድፈር ወይም አስገድዶ የመድፈር ሙከራ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- አዋቂ ሴት አስገድዶ መድፈር
- ታዳጊዎችን አስገድዶ መድፈር (ሴት ወይም ወንድ)፣ ከስጋ ዘመድ ጋር የሚፈፀመውን ወሲብ ጨምሮ
- ቡድናዊ አስገድዶ መድፈር፤ ከአንድ በላይ ግለሰብ ተሳትፎ ከሆነ
- በባልና በሚስት መካከል የሚከሰት የትዳር አጋር አስገድዶ መድፈር
- የወንድ ተገድዶ መደፈር፣ አንዳንዴ ግብረሰዶም በመባል የሚታወቀው

3. **ስነ-ልቦናዊ/ስሜታዊ ጥቃት/ብዝበዛ እና ቸልተኝነት** ለብቻ ወይም በአደባባይ የሚፈፀም የማስገደድ ተግባር ወይም አዋራጅ አባባሎችን መሰንዘር (ለምሳሌ ስድብ/ዘለፋ በቃል ወይም በንግግር ማጥቃት) እና ጭፍን የነፃነት ገፈፋን ያካትታል፡፡

ስነ-ልቦናዊ/ስሜት ነክ ጥቃት በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡ ግለሰብን ማዋረድ፣ ግለሰቡ ማድረግ በሚችለውና በማይችለው ላይ አዛዥ/የበላይ መሆን፣ ከአንድ ግለሰብ መረጃ መሰወር፣ ግለሰቡ ሳይስማማ ሲቀር መቆጣት፣ ግለሰቡ ጎደሎነት እንዲሰማው ሆን ብሎ ማድረግ

(ለምሳሌ ሞኝ ወይም መስህብ የጎደለው)፣ ሆን ብሎ ግለሰብን የማሳፈር ተግባር መፈፀም፣ ግለሰብን ከቤተሰብና ከጓደኞች መለየት፣ ስልክ ወይም ትራንስፖርት እንዳይጠቀሙ መከልከል፣ ገንዘብና ሌሎች ንብረቶችን እንዳይጠቀሙ ማገድ፣ የህፃናት አሳዳጊነትን ሚና የማሳጣት ዛቻ፣ የሰውን እቃ መሰባበር ወይም የሰውን ንብረት ማውደም።
ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ቀደም የተፈፀመ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት በተከሰተበት ወይም የአካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ዛቻ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ የሚፈፀሙ የማስፈራሪያ ድርጊቶችንና የማስገደጃ ስልቶችን ያካትታል።

**መልመጃ 1.4 ድብብቆሽ**

*አመቻቹ የዚህን መልመጃ አሰራር ያስረዷቹኋል። ይህ የክርክር መልመጃ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የመደበቅ ወይም የማለባበስ ሀሳብ መፍጠር የሚያስችላችሁ ሲሆን የሚከሰተውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነትም እንዴት መለየት እንደምትችሉ ትማሩበታላችሁ።*
*ለሁላችሁም የተለያዩ ታሪኮች የሚነገራችሁ ሲሆን ክስተቱን ለመደበቅ/ለማለባበስ ወይም ክስተቱን ለማርገብና ለማጋለጥ እንዲሁም የተከሰተውን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነት ለመጥቀስ መከራከር ለትናንሽ ቡድኖቹ ውሳኔ የሚተው ነው።*
*ይህንን ተግባር ለማጠናቀቅ 20 ደቂቃዎች ያህል የሚወስድ ሲሆን ንቁ ተሳትፏችሁ በጣም አስፈላጊ ነው።*

## ክፍል 3፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠንና የሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች

### 3.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች

ይህ ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ:-

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠንን ማብራራት
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚያስከትላቸውን ኤኮሚያዊ፣ ማህበራዊና ጤናነክ ተፅእኖዎች መግለፅ

**ቁልፍ ክህሎቶች፤**

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠንና የሚያስከትላቸው ተፅእኖዎችን የተመለከተ እውቀት
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች በሚከናወኑ ተግባራት ወቅት እውቀትን የመጠቀም ችሎታ

### 3.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠን

ከሁሉም የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ውስጥ በስፋት የሚከሰተው ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው፡፡ በአለምአቀፍ ደረጃ ከሶስት ሴቶች ውስጥ አንዷ በህይወት ዘመኗ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት እንደሚደርስባት የሚገመት ሲሆን ከአምስት ሴቶች ውስጥ አንዷ ተገድዶ መደፈር (ተገድዶ የመደፈር ሙከራ) ይደርስባታል፡፡ ወንዶችም ቢሆኑ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚደርስባቸው ሲሆን መጠኑና የሚያስከትላቸው የጤና ተፅእኖዎች ግን በሴቶች ላይ ይበልጥ የከፋ ነው፡፡

በቅርብ አጋር የሚፈፀም ጥቃት በስፋት ከሚከሰቱ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥቃት አይነቶች ውስጥ ይገኛል፡፡ በህይወት ዘመናቸው በቅርብ አጋር ለሚፈፀም ጥቃት የተጋለጡ ሴቶች መጠን በጃፓን እስከ 20 % በኢትዮጵያ 70 % ይደርሳል (ኢ.ዲ.ኤች.ኤስ 2011)፡፡ ከ4 - 32 % የሚሆኑ ሴቶች በእርግዝናቸው ወቅት በቅርብ አጋር ለሚፈፀም ጥቃት ይጋለጣሉ፡፡ በቅርብ አጋር የሚፈፀም ጥቃት ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት (4 - 11 %) ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት በስፋት ይከሰታል (14 - 32 %) ፡፡

### 3.3 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች


**መልመጃ 1.5 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ስለሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች ሀሳብ ማጉረፍ**

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች በተመለከተ ሀሳብ እንድታጎርፉ ተጠየቃላችሁ፡፡ አመቻቹ የምትሰጧቸውን መልሶች ይፅፉና በሚከተሉት ክፍሎች ይመድቧቸዋል (1) ጤና (2) ኢኮኖሚ (3) ማህበራዊ እና (4) ሌሎች፡፡ *ይህንን ተግባር ለማጠናቀቅ 15 ደቂቃዎች ያህል ይወስዳል፡፡ የእናንተ ንቁ ተሳትፎና አስተዋፅኦ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡*

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በአዋቂ የጥቃቱ ተጎጂዎችና ጥቃቱ ሲደርስ በቦታው ተገኝተው በተመለከቱ ህፃናት ላይ ውስብስብ ተፅእኖዎችን ያስከትላል፡፡
ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎች/ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ራሳቸውን የመውቀስ (ራስ-ወቀሳ) እና የጥፋተኛነት ስሜት የማሳደር ዝንባሌ አላቸው፡፡ በቤተሰብ፣ በጓደኛና በማህበረሰብ መገለልና ወቀሳ ይደርስባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የጥቃት ተጎጂዎቹን መብት፣ ነፃነት፣ ደህንነት የሚሸረሽር ሲሆን በማህረሰቡ ውስጥ ያለውን የስርዓተ-ፆታ እኩልነት መዛባት ይበልጥ ያጠናክራል፡፡

ከዚህ ባለፈ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በማህበረሰብ ላይ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖ ያሳድራል። የቤት ውስጥ ጥቃትና አስገድዶ መድፈር እድሜያቸው ከ15-44 የሆኑ ሴቶች ከ5-16% ጤነኛ የህይወት አመታትን የማሳጣት አስተዋፅኦ በማድረግ ህመምተኛነትና ሞት እንዲጨምር ምክንያት ይሆናሉ።

በተጨማሪም ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ጤናነክ ተፅእኖዎችን ያስከትላል። በአካላዊ፣ በአእምሯዊና በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡ አካላዊ የጤና ተፅእኖዎች ከመብለዝና መቀደድ ጀምሮ የአካል ክፍሎችን እስከማጣትና ይህንኑም ተከትሎ ለሚመጣ አካልጉዳተኝነት፣ ቅርፀ-ቢስነትና ሞት ሊደርሱ ይችላሉ። አእምሯዊ የጤና ተፅእኖዎችም ድህረ-አደጋዊ የጭንቀት እክል፣ ድባቴ፣ የፍርሀት አባዜ፣ የመሸበር እክል፣ ጭንቀት/ሽብር፣ ራስን መጉዳት፣ ራስን ማጥፋት፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የጥቃት ፈፃሚነት ዝንባሌ ፣ የእንቅልፍ እክሎች፣ ዝቅተኛ ግለግምት፣ የወሲባዊ ዝንባሌ ለውጥ ወዘተ። ስርዓተ-ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ከሚመጡ ወሲባዊና ስነተዋልዷዊ የጤና ችግሮች ውስጥ የዳሌ ብግነት በሽታ፣ የአባለዘር በሽታ/ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የማህፀን በር ካንሰር፣ የወሲብ ትግበራ መስተጓጎል፣ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ፅንስ ማቋረጥ፣ ማስወረድ/በደም መመታት የፅንስ ጉዳት፣ የአፍ ቁስለት እና የመሳሰሉት ይገኙበታል።




**ምንጭ፡-** Heise L, Ellsberg M, Gottemoeller M, *Ending violence against women*. Population Reports, Volume XXVI, No. 4, December 1999.

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶችና ህፃናት ላይ ሞት ሊያስከትል ይችላል። የሞት ውጤቶች የጥቃት ተጎጂዋ በጥቃት ፈፃሚው በመገደሏ የሚፈጠር ቀጥተኛ ውጤት አልያም ከጊዜ በኂላ የሚከሰቱ ጎጂ የጤና ችግሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ በአካላዊ አደጋ ምክንያት የሚፈጠር የአእምሮ ጤና ችግር ራስን ለማጥፋት ሊጋብዝ ወይም ለአልኮል አብዝቶ ጠጪነት ወይም ሞት ለሚያስከትል የስርአተልብና ደምስር በሽታዎች ሊዳርግ ይችላል። ከዚህም ባለፈ በወሲባዊ ጥቃት የሚከሰት የኤች.አይ.ቪ ኢንፌክሽን ለኤድስ ሊዳርግና በሂደትም ወደ ሞት ሊያመራ ይችላል።

## ክፍል 4፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዘርፈ-ብዙ ምላሽ/አቀራረብ

### 4.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች

ይህ ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ፡-

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን/ወሲባዊ ጥቃትን (በተለይ በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚደርሰውን) ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ከወሳኝ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት አስፈላጊ የሆነበትን መሰረታዊ ምክንያት መግለፅ
- ከወሲባዊ ጥቃት (በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚደርሰው) ጋር በተያያዘ የልማዳዊ ደንቦችንና የአሰራር ደንቦችን አስፈላጊነት ማብራራት
- የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂን ማእከል በማድረግ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርአት ሰነድን (SOPs) መሰረታዊ ይዘቶች መግለፅ

**ቁልፍ ክህሎቶች**

- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/የወሲባዊ ጥቃት ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ያለውን ዋጋ የተመለከተ እውቀት
- የወሲባዊ ጥቃት (በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ የሚደርሰው) ዘርፈ-ብዙ የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርአት ሰነድን (SOPs) አጠቃላይ ፅንሰ ሀሳብ መረዳትና ሰነዱን መጠቀም

### 4.2 ዘርፈ-ብዙ ምላሽ

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ትርጉም "ወንዶችና ሴቶች የተሳተፉበትና አብዛኛውን ጊዜ ግን ሴቷ ተጎጂ የምትሆንበት ጥቃት" መሆኑን እና አብዛኛውን ጊዜም "ከሀይል አለመመጣጠን" የተነሳ የሚከሰት መሆኑን እንዲሁም የተለያዩ የጥቃት አይነቶች ማለትም አካላዊ፣ ወሲባዊና ስነልቦናዊ/ስሜታዊ ጥቃት እና ኢኮኖሚያዊ አለአግባብ ተጠቃሚነትና ብዝበዛ ተያያዥና የተሳሰሩ መሆናቸውን መቀበል፤ ለተጎጂዎቹ ፍላጎቶች ሁሉን አቀፍ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑትን ግብአቶችና ሙያዊ እውቀቶች አሟልቶ የያዘ ነጠላ ተቋም አለመኖሩን ማረጋገጥ፤ የጥቃት ተጎጂዎች ቀጥተኛና ሁሉን አቀፍ የእንክብካቤና ድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማስቻልና ከመብታቸው መጣስ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱባቸው የሚችሉትን የረጅም ጊዜ ተፅእኖዎች ለመቀነስ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት (ጤና፣ ፍትህና የማህበራዊ ደህንነት ስርአቶች) ወሳኝ ሚና እንዳላቸው ማረጋገጥ፤ በኢትዮጵያ መንግስት በህገ መንግስቱ ላይና በሌሎች የህግ ማእቀፎች ላይ ሰፍሮ እንደሚታየው በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለማስቀረት ቁርጠኝነት ያለው ሲሆን በዚህም የተነሳ ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ዘርፈ-ብዙ ብሄራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ አቋቁሟል፡፡

ዘርፈ-ብዙ ብሄራዊ አስተባባሪ ኮሚቴው ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርአት ሰነድ (SOPs) ያዘጋጀ ሲሆን የሰነዱ አጠቃላይ አላማም ሁሉንም አይነት ወሲባዊ ጥቃቶች ለመከላከልና ለማስቀረት እንዲሁም ለሴቶችና ለህፃናት ድጋፍ መስጫ ዘርፈ-ብዙ ስልቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ብሄራዊ የመከላከል፣ የክለላና አገልግሎት አሰጣጥ ተስማሚነቶችን እስታንዳርድ ማስጠበቅ ነው፡፡

ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርአት ሰነድ የጥቃት ተጎጂን ማእከል በማድረግ የእያንዳንዱን ወሳኝ ሴክተርና ተዋናይ ሚናና ሀላፊነት ያስቀመጠ ሲሆን ይኸውም ለአስቸኳይ ፍላጎቶች የተሻለ ምላሽ ለመስጠት፣ የረጅም ጊዜ ተፅእኖዎችን ለመከላከልና እንዲሁም የአገልግሎቶች ምላሽ መስጫ መንገዶችን ለማሳየት ነው፡፡

*ለምሳሌ፡*

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎች የሚደረግ ስኬታማ ዘርፈ-ብዙ አቀራረብ ለተጎጂው ጠቀሜታ የሚያተርፍ የወሳኝ ሴክተሮች/ተዋናዮች ተግባራዊ ትስስርና ፍሰት ያለው ግንኙነት ይጠይቃል፡፡ ከወሲባዊ ጥቃት ወይም ብዝበዛ *የተጎዳች* ሴት ወይም ወንድ ራሷን/ሱን ፖሊስ ጣቢያ

ወይም ሆስፒታል ልታቀርብ/ሊያቀርብ ትችላለች/ይችላል፡፡ በቅድሚያ የቀረበው/ችው ፖሊስ ላይ ከሆነ ፖሊስ አስፈላጊውን አሰራሮች ካከናወነ በኋላ የጤና ምርመራ እንዲያካሂዱላት *ተጎጂውን/ዋን ከጤና ተቋም ጋር ያገናኛል፡፡* በሌላ በኩል ደግሞ ተጎጂው/ዋ በቅድሚያ የመጣው/ችው ወደ ህክምና ተቋም ከሆነ አስፈላጊው የእንክብካቤና የህክምና ሂደቶች ከተካሄዱ በኋላ *ተጎጂዉ/ዋን ከህግ አስፈፃሚ/ከፖሊስ ጋር ማገናኘት ይቻላል፡፡*

የተፈፀመው ጥቃት የቤት ውስጥ ጥቃት ከሆነና ተጎጂው/ዋን ከሌላ ተጨማሪ ጥቃት ከመጠበቅ አንፃር ተጎጂው/ዋን *ከድንገተኛ መጠጊያ ወይም መከለያ ተቋም ጋር ማገናኘት* (ከማህበራዊ ጉዳዮች ወይም ከሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር) ግዴታ ይሆናል፡፡ ተጎጂው/ዋ የህግ ድጋፍ ከፈለገችም ተጎጂው/ዋን *ከህግ አካላት ጋር ማገናኘት* (ከአቃቤ ህግ ቢሮ) የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ የጥቃቱ ተጎጂ ታዳጊ ህፃን በሚሆንበትና ክስተቱን በአግባቡ በማይረዳበት አጋጣሚ ደግሞ ህፃኑን/ኗን በህክምና ከሰለጠነ ማህበራዊ ሰራተኛ ጋር (ማህበራዊ ጉዳይ) በማስተሳሰር ህፃኗን/ኑን ለቀጣይ የህግ ሂደቶች ያዘጋጃታል፡፡ በአሁን ሰአት በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትንና በቀጣይነት የሚያጋጥሙትን የጥቃት ተጎጂዎች ለመለየት ማህበረሰብን ማሳተፍ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን እንደነዚህ አይነቶቹን የጥቃት ተጎጂዎች በማስተናገድ ላይም ይሳተፋል፡፡ በዚህ መልኩም ዘርፈ-ብዙ "ሽክርክሪት" (መልመጃ 1.7 ይመልከቱ) ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች በማስተናገድ ሂደት ያሉትን ወሳኝ ክፍተቶች ለማጥበብ የሚያደርገው ጥረት የጥቃት ተራፊዎችን አያያዝ እና ለፍላጎቶቻቸውም ምላሽ የመስጠቱን ስራ የተቃናና ስኬታማ እንዲሆን ያመቻቻል፡፡

### መልመጃ 1.6 አጭር ጥያቄዎችና መልሶች

*ይህንን መልመጃ በየግላችሁ ሰርታችሁ ለማጠናቀቅ 15 ደቂቃዎች ይሰጧችኋል፡፡ ስትጨርሱ አመቻቹ ትክክለኛዎቹን መልሶች ያብራሩላችኋል፡፡*

1. ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች የዘርፈ-ብዙ አቀራረብ አላማ ምንድነው?

2. ጥቃት የደረሰባትን ህፃን ችሎት ከመቅረቧ በፊት አስቀድሞ እንድትዘጋጅ ማድረጉ ያለው አስፈላጊነት ምንድነው? የዚህን ሂደት ሀላፊነት መውሰድ ያለበትስ ማን ነው?

3. እርስዎ ለጥቃት የተጋለጡ ቡድኖችን መጠበቅ በተመለከተ የአካባቢ የአመራር አካላትን (በማህበረሰብ ደረጃ) አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው ብለው የሚያስቡት ለምንድነው?


4. ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን በተመለከተ የጤናው ሴክተር የዘርፈ-ብዙ አቀራረብ አካል የመሆኑ አስፈላጊነት ለምንድነው?

5. ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከልና ምላሽ የመስጠት የአተገባበር ስርአት ሰነድ (SOPs) የሚያስፈልገን ለምንድነው?

**መልመጃ 1.7 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎች "ሸክርክሪት"**

የጥቃት ተጎጂዎቹን ማእከል በማድረግ "ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተጎጂዎች የሚከናወኑ ተግባራት ሸክርክሪት" ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የድጋፍ ክፍሎችን/ቦታዎችን እንድትሞሉ ትጠየቃላችሁ።

*ይህንን መልመጃ በየግላችሁ ስርታችሁ ለማጠናቀቅ 5 ደቂቃዎች አሏችሁ። በማስከተልም አመቻቹ ትክክለኛውን መልሶች ያሳዩዋችኋል። ተሳትፏችሁ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።*



# ክፍል 5፡ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምላሽን በተመለከተ ህጋዊው አውድ እና የሙያ ስነ-ምግባር

## 5.1 የክፍለ ጊዜው አላማዎች

ይህ ክፍለ ጊዜ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ፤

- ○ በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን የተመለከቱ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችን መግለፅ
- ○ የሴቶችንና የህፃናትን መብቶች ለመጠበቅ የተቀረፁ አለምአቀፍ ስምምነቶችንና ሀገራዊ የህግ ማእቀፎችን መግለፅ
- ○ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ወገኖች መብቶች መከበር ለማሻሻል የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን አቅም ማሳደግ
- ○ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከደረሰባቸው ወገኖች እንክብካቤ ጋር በተያያዘ የጤና ባለሙያዎችን የሙያ ስነምግባር ማብራራት

**ቁልፍ ክህሎቶች፡-**

**ግንዛቤ**

- የሴቶችንና የህፃናትን መብቶች ለመጠበቅ የተቀረፁ ሰብአዊ መብቶችን፣ አለምአቀፍ ስምምነቶችንና ሀገራዊ የህግ ማእቀፎችን የተመለከተ እውቀት
- ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መፍትሄያዊ እርምጃዎች ወቅት እውቀትን የመጠቀም ችሎታ

**ክህሎት**

- የሙያ ስነምግባሮችን በሰለጠነ ሁኔታ በተግባር የማዋል ብቃት

## 5.2 ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምላሽን በተመለከተ ያለው ህጋዊ አውድ

አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶችና በአለም ላይ የሚገኙ ሀገራት ህጎች የሲቪልና የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ለበርካታ የሴቶች መሰረታዊና የአሰራር መብቶች እውቅና ይሰጣሉ፡፡ ነገር ግን ሰብአዊ መብቶች በተጨባጭ ይከበሩ ዘንድ የመብቶች ጥሰትንና አለመከበርን ስርአት ባለው መንገድ ማስተካከልና ፈጣን እርምጃ መውሰድ ይጠይቃል፡፡

የጥቃት ተጎጂዎችን መብቶች ጥሰትና አለመከበር ማስተካከልና መፍትሄዎችን መፈለግ መቻል የጤና፣ የፍትህና የማህበራዊ ስርአቶችን መኖርና ተደራሽነት ያለምንም መድልዎ ለሁሉም ማረጋገጥን ታሳቢ ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት ፍትህ ማግኘት፣ ተገቢ ዳኝነትና በህግ ፊት እኩልነት ሴቶችንና ህፃናትን ጨምሮ የእያንዳንዱ ግለሰብ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

የሴቶች መብቶች እኩልነት የተባበሩት መንግስታት መሰረታዊ መርህ ሲሆን በተባበሩት መንግስታት ቻርተር ላይም ሰፍሯል፡፡ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር ላይ በመመስረትም ሁሉም አባል ሀገራት የሴቶችና የወንዶችን እኩል መብቶች ጨምሮ ሰብአዊ መብቶችንና መሰረታዊ ነፃነቶችን አሟልተው እንዲተገብሩ የህግ አስገዳጅነት አለባቸው፡፡ አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች መድበል (International Bill of Rights) እና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌም (Universal Declaration of Human Rights) ተመሳሳይ ሀሳብ የያዙ ናቸው፡፡

በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት አድልዎን የማስወገድ ስምምነት (CEDAW) በተባበሩት መንግስታት አጠቃላይ ጉባኤ እ.ኤ.አ በ1979 ፀድቆ እ.ኤ.አ መስከረም 3/1981 ወደተግበራ ገብቷል፡፡ ኢትዮጵያ ይህንን ስምምነት እ.ኤ.አ ሀምሌ 8/1980 የፈረመች ሲሆን እ.ኤ.አ መስከረም 10/1981 አፅድቃለች፡፡ በሴቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት አድልዎን የማስወገድ ስምምነት (CEDAW) ብዙጊዜ የሴቶች የአለምአቀፍ መብቶች መድበል ተደርጎይወሰዳል፡፡ ስምምነቱየሴቶችን የስነተዋልዶ መብቶች ያስረገጠና ልማዳዊ ደንቦችንና የቤተሰብ ግንኙነቶችን በመቅረፅ ረገድ ባህልና ልማድ ወሳኝ ተፅእኖ አሳዳሪዎች መሆናቸውን ያረጋገጠ ስምምነት ነው፡፡ ሀገራት አንዱን ፆታ የበታች ወይም የበላይ በሚያደርጉ ወይም ለሴቶችና ለወንዶች ፍረጃዊ/ድምዳሜያዊ ሚና በመስጠት ላይ መሰረት ያደረጉ ጭፍን ጥላቻዎችንና ልማዶችን ለማስወገድ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ

የህፃናት መብቶች ስምምነት እ.ኤ.አ በ1989 በተባበሩት መንግስታ አጠቃላይ ጉባኤ የፀደቀ ሲሆን ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ ግንቦት 4/1991 ተቀብላዋለች፡፡

ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ህጎች ወደ ሀገሪቱ የህግ ማእቀፍ የሚለወጡ ሲሆን በዚህም የሀገሪቱ ብሄራዊ ህጎች አካል ይሆናሉ፡፡ በእርግጥም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ 9 (4) "ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል ናቸው" ይላል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት አለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር ተያይዞና መሰረት አድርጎ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት በሁሉም ዘርፎች በሚደረጉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥረቶችና ተጠቃሚነቶች ውስጥ ለሚኖር የወንዶችና የሴቶች እኩልነት ዋስትና ይሰጣል፡፡ ከዚም በተጨማሪ አንቀፅ 13 (2) በህገ-መንግቱ ምእራፍ 3 ("መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች" በሚል ርእስ) ስር ተቀባይነት ያገኙ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች አተረጓጎም ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችና ከሌሎች አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃል-ኪዳኖችና ስምምነቶች ጋር እንደሚጣጣሙ ይገልፃል፡፡

በተጨማሪም ፍትህ ማግኘት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ዘንድ መብት ተደርጎ ነው የሚወሰደው፤ አንቀፅ 37 (1) ሁሉም ዜጎች ፍትህ የማግኘት ዋስትና እንዳላቸው እንዲህ በማለት ይገልፃል "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው"፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ህገ-መንግስቱ በህግ ፊት ለሚኖር እኩልነት እውቅና ይሰጣል (አንቀፅ 25)፤ "ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማናቸውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል [...]"፡፡ ከዚህም በላይ ህገመንግስቱ የሴቶችን እኩልነት አስመልክቶ በአንቀፅ 35 ላይ እንዲህ ይላል "ሴቶች ይህ ህገ-መንግስት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው"፡፡ ይህ አንቀፅ የሴቶች መብት ከጎጂ ልማዶች በመንግስት እንደሚጠበቅ ዋስትና ይሰጣል፤ "ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሯቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ህጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው"፡፡

ከአንድ ሰው የመብት ባለቤትነት ቁልፍ ገፅታዎች መካከል የዛው መጠን መብቱን የማስከበር ወይም የማስጠበቅ ሀላፊነት በሌላ ሰው ላይ ይወድቃል፡፡ የወሲባዊ ጥቃትና የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎች፣ ጥቃት የደረሰባቸውና ምስክሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ታዋቂነት እያገኙ መጥተዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የጥቃቱ ጉዳት በሰዎቹ፣ በቤተሰባቸውና በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ከፍ በማለቱና ሪፖርት የሚደረጉ ጥቃቶችም ቁጥር በመጨመሩ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎችን ሀገራዊ አጀንዳ የማድረግ ጥረቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ታይተዋል፡፡ እነዚህ ጥረቶች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት ለጥቃት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች (ለምሳሌ ህፃናትና ሴቶች) በሰጠው ህገመንግስታዊ ጥበቃ፣ የጥቃት ተጎጂዎችን ፍላጎቶች በተመለከተ ያለው ግንዛቤ መጨመርና እንዲሁም የአሰራር ተጎጂነትን/ተጓዳኝ ተጎጂነትን ለማስወገድ በሚያግዙት ወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ላይ በተካተቱት ማሻሻያዎች ማለትም በፌዴራል ደረጃ ዲፓርትመንቶችን አቀናጅቶ የሚመራ ቡድን በመፍጠር እርምጃና አለምአቀፍ እስታንዳርዶችን ተከትሎ በፖሊስ ሰራዊት፣ በአቃቤ ህግና በፍርድ ስርአቱ ውስጥ እየተካሄዱ በሚገኙት ተጨባጭ ለውጦች ተንፀባርቀዋል፡፡

ለወንጀል ተጎጂዎች ትኩረት በመስጠት የጥቃት ፈፃሚ መብቶች አለአግባብ አደጋ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ የሚለውን ወቀሳ ከወዲሁ ለማስወገድ ቁልፉ ዘዴ በተጎጂዎቹ ላይ ከሰብአዊ መብቶች አንፃር ማተኮር ሲሆን ይኸውም እነዚህ መብቶች የጥቃት ተጎጂን እና የጥቃት ፈፃሚን ሰብአዊ መብቶች በእኩልነት በማስከበር ቁርጠኝነት ላይ የተመሰረቱ ናቸውና፡፡ ሚዛናዊነቱ በአስተማማኝ ደረጃ ሊጠበቅ የሚችለው ተጠቂዎችን ያማከለ ወንጀል መከላከያ ፕሮግራም ቀረፃ ላይ ከፍተኛ ሀይል በማፍሰስ ነው፡፡ ይህ ፕሮግራም ለተጎጂው ውጤታማ ድጋፍ በመስጠትና ተጎጂውን በማብቃት ላይ በእጅጉ ማተኮር

የሚገባው ሲሆን ይህ ደግሞ የየትኛውንም ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ወንጀለኛ መብቶች ሳያንድሉ ለተጎጂዎች ሰብአዊ መብቶች ቅድሚያ መሰጠቱን ያሳያል፡፡

## 5.3 ለስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት/ወሲባዊ ጥቃት ምላሽ ለመስጠት የባለሙያዎች የሙያ ስነ-ምግባር

በህግና በስነ-ምግባር መካከል መሰረታዊ ትስስር አለ፡፡ ህግ ማለት ህጉን ያወጣው አካል በይፋ ያሳወቀው ወይም ያዘዘው የጠባይ ወይም የድርጊት ደንብ ሲሆን ስነ-ምግባር ደግሞ ከአንድ ባለሙያ የሚጠበቁትን ብቁ ባህሪያት የሚገልፅ ነው፡፡ በሌላ አባባል ስነ-ምግባር ማለት በአንድ ሁኔታ ውስጥ ከህግ ግንዛቤ ባሻገር የአንድ ድርጊት ትክክለኛነት እና ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ ለስነ-ምግባራዊ ባህሪይ መሰረት ሆኖ እንዲያገለግል ግብረገባዊ እሴቱ ከፍተኛ አፅንኦት ይሰጠዋል፤ ስለዚህም የቤተሰብ፣ የባህልና የማህበረሰብ ተፅእኖ ያርፍበታል፡፡

ስነ-ምግባር በየትኛውም የህግ ስርአት ውስጥ  መሰረታዊ የህግ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በጤናው ዘርፍ ያለው አተገባበር ከህመምተኛና ከታካሚ ተግባቦትና ድርጊቶች ጋር በተያያዘ ሊፈተሽ ይችላል፤

- *የስምምነት ፈቃድና ቴክኒካዊ መረጃ መስጠት፡* ትኩረት መስጠት፣ በንቃት ማዳመጥ፣ ማብራራትና በትክክል መረዳታቸውን ማረጋገጥ እና የስምምነት ፈቃድ መጠየቅ (እንደተገቢነቱ የቃል ወይም የፅሁፍ) በስራ ላይ ለሚውል ስነምግባር አቢይ ግብአቶች ናቸው፡፡
- *የታካሚ-የሀኪም ምስጢራዊነት፤* ግለሰባዊ የጤና መረጃ የሚገኝ በመሆኑ የታካሚውን ችግር ሚስጢራዊነት ማስጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡
- *አክብሮትና እምነት፤* ታካሚዎችን በትህትናና በአክብሮት መያዝና የርህራሄና የተንከባካቢነት አቀራረብን ማሳየት የሙያ ስነምግባር ክፍሎች ናቸው፤ እምነትን ማፍረስና አክብሮት መንሳት ህክምናውንና የሚሰጡትን የህክምና ምክሮች በታዘዘው መሰረት አለመተግበርን የሚያስከትል ሲሆን ይህ ደግሞ አሉታዊ ውጤቶች አሉት፡፡

### መልመጃ 1.8 ምሳሌያዊ ታሪክ

***ታሪክ 1፡*** *አንዲት የ63 አመት አዛውንት ሴት ወደ ጤና ተቋም ይሄዱና የማያቋርጥ ሀይለኛ ራስምታት እንደሚያማቸውና ከብልታቸውም ፈሳሽ እንደሚፈሳቸው በስራ ላይ ለነበረ ሀኪም ችግራቸውን ያስረዳሉ፡፡ ሀኪሙም ሴትየዋ የገለፁዋቸውን ችግሮች ታሪክ በአጭሩ ከወሰደ በኂላ ደም ግፊታቸውን ይለካል (ውጤቱ ከእድሜያቸው ጋር ሲስተያይ ጤነኛ ነው) እንዲሁም የአባለዘር በሽታ ህክምና መድሀኒት ያዝላቸዋል፡፡ ሴትየዋም የምርመራ ውጤታቸውን እንዲነግራቸው ሀኪሙን በትህትና ይጠይቁታል፡፡ ሀኪሙም "እማማ፥ ምንም እንኳን በዚህ እድሜዎ እንደዚህ አይነት ነገር ከእርስዎ እድሜ ባልጠብቅም የአባለዘር በሽታ ያለብዎት በመሆኑ የህክምና መድሃኒት አዝዤልዎታለሁ" በማለት ይመልስላቸዋል፡፡*

*ለጥያቄዎቹ የየግላቸሁን መልስ ለመስጠት 5 ደቂቃዎች አሏችሁ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አመቻቹ መልሶቹን ያብራሩላችኂል፡፡*

1. የስነምግባር ጥሰት የታየባቸውን አጋጣሚዎች ለዩ፡፡ በታሪኩ ውስጥ ስነምግባር ጉድለት ያለባቸውን ባህሪያት አጽንኦት ስጡባቸው፡፡
2. የጎደሉት ወይም መስተካከል የሚገባቸው ባህሪያት የትኞቹ ናቸው?
3. በሀኪሙ ቦታ እርስዎ ቢሆኑ ኖሮ አቀራረብዎ እንዴት ይሆን ነበር?

## የሞጁል 1 ማጠቃለያ

ይህ ሞጁል ስለ ስርዓተ-ፆታ እና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ፅንሰ-ሀሳብ አጠቃላይ ማብራሪያ የሰጠ ነው፡፡ የተለያዩ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነቶች ተለይተው የቀረቡና የተብራሩ ሲሆን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መጠንና እነዚህ ጥቃቶች ጥቃት በደረሰባቸው/በተጎጂዎች ላይ የሚያስከትሏቸው ከባድ ተፅእኖዎችም አፅንኦት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃት/ለወሲባዊ ጥቃት መፍትሄ የመፈለጉ ጥረት ዘርፈ-ብዙ አቀራረብን መከተል እንደሚገባው የተብራራ ሲሆን የተለያዩ ዘርፎችም ተለይተዋል፡፡

በተጨማሪም የሰብአዊ መብቶች ፅንሰ-ሀሳብና ከሴቶች የጤና መብቶች ጋር ያለው ትስስር፤ በተለይም ከጤና አንፃር የሴቶችን ሰብአዊ መብቶች አሟልቶ ለመረዳት የሚያስችሉ ወሳኝ ፅንሰ-ሀሳቦች የተብራሩ ሲሆን ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትና ወሲባዊ ጥቃት የሴቶችን ሰብአዊ መብቶች መጣስ ተደርጎ መወሰድ እንዳለበትም አፅንኦት ተሠጥቶበታል፡፡ ሞጁሉ የሴቶች ሰብአዊ መብቶች በሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውም አይነት አድልዎን የማስወገድ ስምምነት (CEDAW) እና በህፃናት መብቶች ስምምነት (CRC) ላይ መስፈራቸውንና እነዚህ አንቀጾችም የኢትዮጵያ የህግ ስርአት አካል መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን መብቶች በተግባር በማዋልና በማስከበር ረገድ የኢትዮጵያ መንግስት ያለው ሚና አፅንኦት ተሰጥቶበታል፡፡

## የተሳታፊዎች ግለ-ምዘና

- ❖ ምን ተማሩ?

- ❖ ምን አይነት እውቀቶችንና ክህሎቶችን ማሻሻል ቻሉ?

- ❖ መሻሻል ይቀረዋል የሚሉት እውቀትና ክህሎት ምንድነው?